# የኢትዮጵያ ሥልጣኔ መነሻው ፥ ጉዞውና መድረሻው

## ጌታቸው ኃይሌ

የዓባይ ወንዝ ከምንጩ ላይ ትንሽ ነው ፤ ከብዙ የኢትዮጵያ ታላላቅ ወንዞች አይበልጥም ። ኢትዮጵያን ሲለቅ ግን ትልቅ ሆኖ ነው ። ምንም እንኳ"ዓባይ" ቃሉ አንስታይ ጾታ ("ትልቂት" ማለት) ቢሆንም ወንዙ በዚህ ስም የተጠራው ይኸንን ትልቅነቱን ለማመልከት ሳይሆን አይቀርም ።

የዓባይን ግልገልነትና ዓቢይነት ያነሣሁት ለሥልጣኔ ልደትና እድገት ምሳሌ እንዲሆነኝ ነው ። የኢትዮጵያ መንግሥት ይዞት የሚጓዘው ሥልጣኔ የተወለደው የኢትዮጵያ መንግሥት እተወለደበት ቦታ ነው ፤ ጽራዕ ወይም ትግራይ ውስጥ ። ሥልጣኔው በዚያና በዚህ ተጉዞ ፥ ተጉዞ እየዳበረ መንግሥታዊ ማእከላችንን አዲስ አበባ ላይ ካደረግነው ከእኛ ዘመን ደርሷል ። የዓባይ ወንዝ ሲጓዝ ከየቦታው የሌላ ወንዞች ውኻ እየተመገበ እንደገዘፈ ሁሉ ፥ የኢትዮጵያ ሥልጣኔም መንግሥት እጁን ከዘረጋበትና ማእከሉ ካደረገበት ቦታ ሁሉ ምግብ እያገኘ ገዝፏል ። መግዘፍ ብቻ ሳይሆን መልኩም በመጠኑም ቢሆን ተለውጧል ። ለምሳሌ ፥ ቀጣዩ ሥልጣኔ ሲጀመር በሕዝብና በመንግሥት ደረጃ የመጻጻፊያው ቋንቋ ግዕዝ ነበር ፤ አሁን አማርኛ ሆኗል ። ይኸ አንድ ግዙፍ ለውጥ ነው ። ግን ጨርሶ ሙጥጥ ብሎ አልተለወጠም ፤ ቋንቋው ቢዳከምም ፊደሉ ቀጥሏል ፤ ቋንቋውም ቀርቶ አልቀረም ። የሚሠራበት ቦታ አለ ።

የዚህ የኢትዮጵያ ሥልጣኔ ባለቤቶች እነማንናቸው? "ሥልጣኔው የዳበረው መንግሥት እጁን ከዘረጋበትና ማእከሉ ካደረገበት ቦታ ሁሉ ምግብ እያገኘ ነው" ካልን ፥ ባለቤቶቹ መንግሥት እጁን በዘረጋበትና ማእከሉ ባደረገበት ቦታ ሁሉ የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ናቸው ። ምንጮቹ የመዘገቡትን የአክሱምን ፥ የአደፋን (የላስታን) ፥ የመርዓዴን (የአምሐራ-ሸዋን) ፥ የጎንደርን ፥ የአዲስ አበባን አስተዋፅዖ ማን ይክዳል? መነሻው ፥ እድገቱና መድረሻውስ አይካድም ፤ ግን ማን ወለደው?

ልደቱ ትግራይ ውስጥ ከሆነ ወላጆቹም እትግራይ ውስጥ ነበሩ ማለት ነው ። ግን ትግራዮች ነበሩ ማለት ነው? የጎንደርና የአዲስ አበባ ሥልጣኔ የተወላጆቹ ሥልጣኔ ነው ካልን የአክሱምን ሥልጣኔም የወለዱት ትግራዮች ናቸው ማለት ይቻላል ። ሊሆን ይችላል ፤ ሆኖም ፥ የታሪክ ሂደት እንዲህ አይደለም ። አንድ ከተማ ሲመሠረት ባህልንና ሥልጣኔን ለማዳበር ከተወላጆቹ ይልቅ መጤዎቹ ያመዝናሉል ። ከተማ የሩቅ ሰዎችን ይስባል ። ጀርመኖች "በበርሊን ከተማ የተወለደ

በርሊናዊ የለም" የሚል ተረት አላቸው ። ለምሳሌ ፥ አክሱም ላይ የሳባውያን ሥልጣኔ ዳብሮ ነበር ። አዳባሪዎቹ የጠፉት ሳባውያን እንጂ ትግሬዎች አልነበሩም ። ቋንቋቸው ይመሰክራል ።

የሥልጣኔያችን አስኳል ሳባውያን ከጠፉ በኋላ የተተካው ግዕዝ ነው ። ግዕዝ ከብዙ ቋንቋዎች አንዱ ነበረ ። ባለቤቶቹ አግዓዝያን ይባሉ ነበረ ። የኢትዮጵያም ስም ብሔረ ግዕዝ ነበረ ። (ኢትዮጵያ የሚለውን ስም የግሏ ያደረገችው በኋላ ነው ።) አገሪቷ በስማቸው የተጠራችው ያቀኗትና የወረስነውን የመንግሥት ሥልጣኔ የፈጠሩት እነሱ ቢሆኑ ነው ። ቋንቋቸውን የጽሑፍና የዕውቀት ቋንቋ ያደረጉትም ብሔራዊ ቋንቋ ስለነበረ ነው ለማለት ይቻላል ። ሌላ ቋንቋ የሚናገሩም ለመጻፍና ዕውቀት ለማግኘት ሲፈልጉ የአግዓዝያንን ቋንቋ እየተማሩ በእነሱ ቋንቋ በግዕዝ ይጽፉ ነበር ። ይህም ትግራዮችን ፥ አማሮችን ፥ ሌሎችንም ይመለከታል ። በአፍ መፍቻ ቋንቋ ላይ ብሔራዊ ቋንቋ ተምሮ በዚያ ቋንቋ መማርና መጻፍ አዲስ ነገር አይደለም ።

ለመሆኑ ፥ አገር አቅንተው ቋንቋቸውንና ሥልጣኔቸውን ያወረሱን አግዓዝያን እነማን ነበሩ? ልጆቻቸው አሁንስ አሉ ወይ? አግዓዝያን ከብዙ ነገዶች አንዱ እንደነበሩና አገር አቅንተር ሥልጣኔ መሥርተው አሁን እንደጠፉ እንጂ ከዚህ የበለጠ ስለእነሱ የሚታወቅ ነገር የለም ። አንድ ነገድ ጠፋ ሲባል ልጆቹ የአባቶቻቸውን ቋንቋ መናገር አቆሙ ማለት ነው ። በኢትዮጵያ ውስጥ እንደ ሳባውያን ፥ እንደ ጋፃራ ፥ እንደሃርላ ያሉ ብዙ ነገዶች ጠፍተዋል ። አግዓዝያንም እንደነሱ ጠፍተዋል ። "የሉም ፤ ጠፍተዋል" ስንል በግዕዝ ቋንቋ አፉን የሚፈታ ነገድ የለም ማለታችን ነው እንጂ ደማቸው ከምድረ ኢትዮጵያ ደርቋል ማለት አይደለም ። ሥልጣኔቸውን ግን ሁላችንም እኩል ወርሰን እኩል አዳብረነዋል ። ኣሁን ካሉት የኢትዮጵያ ነገዶች ውስጥ አንዱ ተለይቶ የአግዓዝያን ወራሲ እኛ ነን ሊል አይችልም ። ግዕዝን የሚመስል ቋንቋ ያላቸው ነገዶች ሁሉ ዘመዶቻቸው ናቸው ። ቋንቋቸውን ቀድሞ ይዞና በይበልጥ መጠቀም በቀጥታ ወራሲነት መብት ይሰጡ ቢሆን ግን አማርኛ ተናጋሪዎችን ማንም አይቀድማቸውም ። ከግዕዝ ቀጥሎ በግዕዝ ፊደል የተጻፈ አማርኛ ነው ።